
# <u>ኮሎኔል  አስናቀ  እንግዳ</u>

***ጥር ፮ ቀን ፲፱፻፮ ዓ/ም ጎንደር፣ኢትዮጵያ***
***ግንቦት ፳፩ ቀን ፪ ሺህ ፱ ዓ/ም***
***አርሊንግተን፣ ቨርኒያ፤ አሜሪካ***



# <u>Colonel Asnake Engida</u>

***Jan. 14, 1914, Ethiopia – May 28, 2017, USA***

# የክቡር ኮሎኔል አስናቀ እንግዳ አጭር የሕይዎት ታሪክ፤

ኮሎኔል አስናቀ እንግዳ ከአባታቸው ከአቶ እንግዳ ገብረ-ማርያም እና ከእናታቸው ከወ/ሮ ውበቴ ገብረ-ሥላሴ በጎንደር ክፍለ-አገር፣ በደብረ-ታቦር አውራጃ አየር-ማርያም ደብር በጥር ፯ ቀን ፲፱፻፮ ዓ/ም ተወለዱ።

ኮ/ል አስናቀ ለውድ አገራቸው የነበራቸውን ፍቅር፣ ኢትዮጵያዊ ወኔና ቁርጠኝነት ሃ ብለው የጀመሩት ገና በለጋ ዕድሜአቸው ነበር። ጊዜው ፋሽስት ጣልያን ኢትዮጵያን በግፍ የወረረበት ስለነበር ወጣቱ አስናቀ ወደ ጎንደር በመሄድ የጀግናውን የደጃዝማች አያሌው ብሩን ጦር ተቀላቅለው ለአገራቸውና ለሕዝባቸው ነፃነትና ክብር በተደረገው መራር የአርበኝነት ተጋድሎ ቀጥታ ተሣታፊ በመሆን ጠላትን ተዋግተዋል።

አፄ ኃይለ-ሥላሴ ወደ ሱዳን መግባታቸው ሲሰማ፣ ትንታጉ አስናቀ ወደዚያው ተጉዘው ሶባ በተባለው ቦታ ወታደራዊ ሥልጠና የተሰጠውና በሻለቃ (በኋላ ጀኔራል) ዊንጌት ይመራ የነበረውንና የጌዴኦን ኃይል በመባል ከታወቀው ልዩ የጦር ክፍል ጋር በመሆን ወደ-አገራቸው ተመልሰው በመግባት አርበኞቻችን አገራቸውን ከጠላት ነፃ ለማውጣት ባደረጓቸው የሞት-የሽረት ፍልሚያዎች ተካፋይ ሆነው የኢትዮጵያን ትንሳኤ ካስገኙ አኩሪ የአገር ባለውለታዎች አንዱ መሆን በቅተዋል።

ጣልያን ተቸንፎ ከአገር ከተባረረና አገራቸው ኢትዮጵያም ነፃነቷን ካስመለሰች በኋላ ከውትድርና ሙያ ወጥተው ለጥቂት ዓመታት በመጀመሪያ ጎንደር ቀጥሎም ደሴ ከተማ በንግድ ሥራ ቆይተዋል። ሆኖም በ፲፱፻፴፭ ዓ/ም በትግራይ ክፍለ-አገር እንደርታ አውራጃ የተቀሰቀሰውና በራያ፣ በክልዕተ-አውላሎና በተንቤን አውራጃዎች የተስፋፋው 'ወያኔ' በመባል የሚታወቀው የሕዝብ

አመጽ በመከሰቱ ምክንያት የንጉሠ-ነገሥቱ መንግሥት ይኽንኑ ችግር ለመቋቋም ወታደራዊ ሥልጠናና ልምድ ያላቸው ዜጎች እንዲከቱ ባስተላለፈው ትእዛዝ መሠረት ኮ/ል አስናቀ ጦሩን ዳግም ተቀላቅለው በኮሎኔል (በኋላ ጄኔራል) ኢሳኢያስ ገብረ-ሥላሴ መሪነት የተሰጣቸውን አካባቢውን የማረጋጋት ወታደራዊ ተልእኮ ተወጥተዋል። ከጥቂት ዓመታት በኋላ አዘዞ ከተማ ይገኝ በነበረው የስምንተኛ ብርጌድ ጦር የአስተዳደር መኮንን ሆነው አገልግለዋል።
በመቀጠልም ወደ አዲስ አበባ ተዛውረው በስንቅና ትጥቅ መኮንንነት ሠርተዋል።

በትጋታቸውና በወታደራዊ ችሎታቸው ተመርጠው ቀዳማዊ ኃይለ-ሥላሴ ጦር ትምህርት ቤት በመግባት የአሥረኛው ምድብ (ኮርስ) አባል ሆነው በ፲፱፻፴፰ ዓ/ም በመኮንንነት መለያ ቁጥር 805 ተመርቀዋል።



ተስፋፊው የሱማሌ መንግሥት በኢትዮጵያ ላይ እያደረሰ የነበረው ትንኮሣ ከጊዜ-ወደ-ጊዜ እያዬለ በሄደበት ጊዜ ኮ/ል አስናቀ የሦስተኛ (አንበሣው) ክፍለ-ጦር የስንቅና ትጥቅ መምሪያ ዋና ኃላፊ ሆነው በከፍተኛ ብቃትና ትጋት አገራቸውን አገልግለዋል።

በማይናወጥ የአገርና የወገን ፍቅር የታነጹት ኮ/ል አስናቀ እንግዳ ኢትዮጵያ ባኅላዊ መሠረቷን ሣትለቅና አኩሪ

እሴቶቿን ጠብቃ ሕዝቧ ዘመናዊ የፍትኅና የእኩልነት ሥርዓት ባለቤት እንዲሆን በነበራቸው ከፍተኛ ምኞት የአስተዳደር ለውጥ እንዲኖር ያላሰለሰ ጥረት ማድረግ የጀመሩት በሠራዊቱ ውስጥ እያሉ ነበር። በመሆኑም ይኸንኑ ቀና ዓላማ ከሚጋሩ ተቆርቋሪ ወገኖች ጋር የሚያደርጉት ምክክር በንጉሠ-ነገሥቱ መንግሥት ባለመወደዱ በመጀመሪያ ከእነ ፊታውራሪ ኃይሉ ክብረት ጋር በመንግሥት ላይ አሲረሃል በመባል ለእስር ተዳርገዋል። ከዚኽ የመጀመሪያ ዙር እስር ከተፈቱ በኋላ በሠራዊቱ ውስጥ የሚሰጡትን ሙያዊ አገልግሎት በመቀጠል ላይ እያሉ በታኅሣስ ፲፱፻፶፫ ዓ/ም ከተደረገው ወታደራዊ የመፈንቅለ-መንግሥት ሙከራ ጋር በተያያዘ ለሁለተኛ ጊዜ ለእስር ተዳርገው ከአምስት ዓመታት ተኩል በኋላ ተለቀዋል። ከእስር ከተፈቱ በኋላ ወደሚወዱት የጦር ክፍላቸው አልተመለሱም።

ቀደም-ሲል በአንድ በኩል በሠራዊቱ ውስጥ በነበራቸው ኃላፊነት ከቦታ-ቦታ በመዘዋወር፤ በሌላ በኩል በያዙት የፖለቲካ አቋም ምክንያት ለእስር በመዳረጋቸው ለቤተሰባቸው ቅድሚያ ለመስጠት ሁኔታዎች አመቺ አልነበሩም። በተለይም ለሁለተኛ ጊዜ በታሰሩ ጊዜ ደሞዛቸውም ስለታገደባቸው አምስት ሕጻናት ልጆቻቸውና ውድ ባለቤታቸው በማያስጠይቃቸው ጉዳይ ያለ እረዳት እንዲቀሩና ለችግር እንዲዳረጉ እንደተፈረደባቸው ይቆጠራል።

ኮ/ል አስናቀ ከእስር ሲፈቱ በጎንደር ክፍለ-አገር በመተማ አቅራቢያ የእርሻ ልማት ላይ በመሠማራት ተግተው ሠርተው በማሠራት አዲስ የሕይዎት ምዕራፍ ጀመሩ። በእርሻ ተግባር ላይ መሠማራታቸው ግን ለኑሮ ብቻ ሣይሆን በውስጣቸው ከልብ የሚያምኑበትን ለሕዝባዊ ሥርዓት ለውጥ እውን መሆን ለሚደረግ ትግል መደራጀትን ያዘለ እቅድ ነበር። አዲሱ የእርሻ ልማት ጥረታቸው በመጀመሪያው ዓመት ላይ እጅግ አመርቂ

ውጤት ያስገኘ ቢሆንም፣ ብዙም ሣይቆይ የየካቲት ስድሣ-ስድስት ሕዝባዊ የለውጥ እንቅስቃሴ በመቀስቀሱና ያንንም ተከትሎ ደርግ ባወጣው የመሬት ፖሊሲ ምክንያት የጀመሩት ሥራ ሊቀጥል አልቻለም።

ኮ/ል አስናቀ የኢትዮጵያ ሕዝብ በአንድነት ተነስቶ ለለውጥ ያደረገውን እንቅስቃሴ በመሠረተ- አሣቡ ቢደግፉትም፣ ደርግ በተከተለው ጥራዝ-ነጠቅ የፖለቲካ ቅኝትና አጠቃላይ አምባ-ገነናዊ አገዛዝ ላይ ደስተኛ አልነበሩም። ያን ስሜታቸውንም በተለመደው ቀጥተኛ ባኅሪያቸው በደርግ አመራር ላይ ለነበሩና ለሚቀርቧቸው ግለሰቦች፣ በተለይም ከቦይ-ስካውትነት ጀምሮ ለወታደራዊ ሙያ እስኪበቃ በቅርብ ለሚያውቁት ለሻለቃ መንግሥቱ ኃይለ-ማርያም በግልጥ ለማስረዳት ጥረት አድርገዋል።

አዲሶቹ የደርግ መሪዎች ግን አገሪቱን ወደ ጥፋት እንዳይወስዷትና ሕዝብም መብቶቹን ለማስከበር ያለውን ተስፋ ከንቱ እንዳያስቀሩ የሚሰጣቸውን ምክር ለመስማት ፈቃደኛ ሆነው አልተኙም። እንዲያውም የኮ/ል አስናቀን አርቆ አስተዋይነት፣ ብልህነትና ከሁሉም በላይ ለሥልጣንም ሆነ ለንዋይ ወይም ለማንኛውም ዓይነት የግል ጥቅም ሊደለሉ የማይችሉና ከምንም በላይ የሕዝብና የአገርን ጥቅም የሚያስቀድሙ መሆናቸውን ካለመረዳት ይመስላል፣ በፈለጉት ከፍተኛ የመንግሥት የሥራ ኃላፊነት እንዲመደቡ፣ ቢያንስ የአገሪቱን ብሔራዊ/ሕዝባዊ ጦር በአዲስ መልክ አደራጅተው እንዲመሩ ሻለቃ መንግሥቱ ደጋግሞ እንደጠየቃቸው ይታወቃል።

በደርግ ግብዝ መሪዎች ተስፋቸውን ያሟጠጡት ኮ/ል አስናቀ ዳግመኛ ቤተሰባቸውንና ቤት-ንብረታቸውን ትተው በመጀመሪያ በጭልጋ አውራጃ ከታዋቂው አርበኛ ከፊታውራሪ አዬለ ተሰማ (አባ-ጓዴ) እና በወቅቱ በአካባቢው የትጥቅ ትግል እንቅስቃሴውን ከጀመረው ኢሕአፓ/ሠ ጋር በመሆን የሥርዓት ለውጥ ትግላቸውን


ከገጠሩ ወገናቸው ጎን ተሠልፈው መቀጠልን ምርጫቸው አደረጉ። በስድሣ-ስድስት ዓመታቸው የልጅ-ልጆቻቸው ከሚሆኑ ጋር በመሠለፍ ዳግም የአረበኝነት ትግላቸውን በቆራጥነት የቀጠሉት አገር-ወዳዱ ኮ/ል አስናቀ እንግዳ በአርማጭሆና በተለያዩ አካባቢዎች እየተዘዋወሩ ሕዝብን በመቀስቀስና በማደራጀት ረገድ ከፍተኛ ሚና ተጫውተዋል።




ከተለያዩ አውራጃዎች የመጡ ተወካዮች በተካፈሉበትና ከኅዳር ፲ እስከ ፲፪ ፲፱፻፸፩ ዓ/ም በተደረገ የሕዝብ ጉባዔ የተመሠረተውን የኢትዮጵያ አገር-ወዳዶች ዴሞክራሲያዊ ድርጅት (ኢአወዲድ) በማደራጀት ግንባር-ቀደም ሚና ከተጫዎቱት ዋነኛ ሰዎች አንዱ ሲሆኑ የድርጅቱም ምክል ሊቀ-መንበር ሆነው ተመርጠው አገልግለዋል።

ትግሉ አድማሱን እያሠፋና እየተጠናከረ እንዲሄድ ለማስቻል የኢትዮጵያ አገር-ወዳዶች ዴሞክራሲያዊ ድርጅትን ከሌሎች ተመሣሣይ አቋም ካላቸው ድርጅቶች ጋር ለማዋሃድ በተደረጉ ጥረቶች ሁሉ በማደራጀትና መሪ በመሆን ኃላፊነታቸውን ተወጥተዋል። በዚኽ ረገድ፣ የኢትዮጵያ አገር-ወዳዶች ዴሞክራሲያዊ ድርጅት

በመጀመሪያ ከኢትዮጵያ ዴሞክራቲክ ኅብረት (ኢዴኅ) አንድ ክፍል ጋርና ከሌሎች ቡድኖችና ግለሰቦች ጋር በመዋሃድ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ዴሞክራሲዊ ግንባርን (ኢብዴግ)፣ በመቀጠልም ኢብዴግን በውጭ-አገር (በተለይም በአሜሪካና በአውሮጳ) ከሚገኙ ቡድኖች ጋር በመዋሃድ የኢትዮጵያ ሕዝብ ዴሞክራቲክ አንድነትን (ኢዴአ)፣ ከዚያም ክተት-ኢትዮጵያን መበሥራችነትና በአመራር አገልግለዋል።





በኢሕአፓ ቀጠና-ሁለት (ሪጂን 2) በመባል በሚታወቀው በአርማጭሆና በአካባቢው የትጥቅ ትግል ያደርግ የነበረው ኢሕአሠ በውስጥ እክሎች ምክንያት እንቅስቃሴው ለጊዜው ሲደናቀፍና ሠራዊቱም ለጊዜው ከቀጠናው ሲወጣ ከሱዳን ድንበር ብዙ ሣይርቅ እንዲቀበር የተደረገው መሣሪያ ወጥቶ የአገር-ወዳድ ታጋዮችና የትግሉ አካልና አጋር የሆነው ሕዝብ እንዲታጠቀው ኮ/ል አስናቀ ያደርጉት ሊያስመሰግንና ሊያኮራ የሚገባ ጥረት በድርጅቱ (ኢሕአፓ/ሠ) አንዳንድ የቀጠናው አመራር አባላት በነበሩ ግለሰቦች አሣፋሪ ጥቆማ በሱዳን መንግሥት እንዲታሠሩና ቆራጥ ታጋዮች በክቡር መስዋዕትነታቸው ያስገኙት መሣሪያም በባዕዳን እጅ እንዲወድቅ የተደረገው የክህደት ተግባር ከልብ ቢያሣዝናቸውም፤ ለትግሉ የነበራቸውን ቁርጠኝነትና መንፈሳዊ ጥንካሪያቸውን ግን ሊገታው አልቻለም።

እንዲያውም ከቅርብ የትግል አጋሮቻቸው ጋር ከሱዳን ተመልሰው ወደ አርማጭሆ በመግባት የአገር-ወዳድ ድርጅትን መልሶ በአዲስ መልክ በማቋቋም፣ የሕዝብ አለኝታና መመኪያ በሆኑት የድርጅቱ የአገር ውስጥ እንቅስቃሴ ቆራጥ መሪዎች በሻለቃ ዘለቀ ጀምበር፣ በሻለቃ በሪሁን ገብረየሱስ እና በሻለቃ ደሴ አያልነህ የበላይ ተጠሪነት በማዋቀር ድርጅቱ ሕዝባዊ መሠረቱን አጠንክሮ እንዲቀጥል ማድረግ ችለዋል።



የአገራቸውና የሕዝባቸው ጉዳይ እረፍት የማይሰጣቸው አርበኛውና ቆራጡ የአንድነትና የመብት የዕድሜ-ልክ ታጋይ ክቡር ኮ/ል አስናቀ ከትግል ጓደኞቻቸው ጋር ሆነው በመሠረቷቸውና መሪ ሆነው ባገለገሉባቸው የፖለቲካ ድርጅቶች ሣይወሰኑ፤ በተለይም የደርግ አገዛዝ የመጨረሻ ዓመታት የኢትዮጵያ እጣ-ፈንታ አንድነቷን በሚፈታተኑ ኃይላት እጅ ወደ መውደቁ እያመራች መሆኑን በቁጭት ከተገነዘቡ የቀድሞ የሠራዊቱ አባላት ጋር በመሆን ‘ነፃ የኢትዮጵያ ወታደሮች ንቅናቄ’ን በማቋቋም መለዮ-ለባሹ የአንድ ፈላጭ-ቆራጭ ግለሰብ ተከታይ ሣይሆን አገሩ ያለችበትን አደገኛ ይዞታ ተረድቶ እንዲደራጅና አገሩን ከመከፋፈል እንዲያድን በተደረገው ጥረት ንቅናቄው የተቋቋመበትን መሠረታዊ ዓላማ እስከሣተበት ጊዜ ድረስ በተለመደው ቅን እና ትጉ ባኅሪያቸው የሚቻላቸውን ሁሉ አድርገዋል።

ደርግ ሲወድቅ የተፈራው የአገር መከፋፈል አደጋ እውን እየሆነ በመጣበት ጊዜ፣ ለአንድነት የቆሙና የሚታገሉ ክፍሎች አንድ ላይ እንዲቆሙ፣ የውጭ መንግሥታትም ኢትዮጵያን ሚየጎዳ የተሣሣተ አቋም እንዳይዙ፣ ወዘተ... በሰላ ብዕራቸውና በትንታግ አንደበታቸው አቤቱታ-ቸውንና ተማጽኗቸውን ያለመሰልቸት ከማቅረብ አልተቆጠቡም።



ታዋቂ ኢትዮጵያውያንን አሰባስበው ‘ጉባዔ አበው’ የሚባል ድርጅት በማቋቋም የአንድነት ኃይሎች አቅማቸውን አስተባብረው አገር-አድን እንቅስቃሴ እንዲያደርጉ ከፍተኛ ጥረት አድርገዋል።

በአገር-ውስጥና ከአገር-ውጭ የሚገኙ የፖለቲካ ድርጅቶች በጋራ የመሠረቱት የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት ሲቋቋም እነ ክቡር ልጅ ሚካኤል እምሩን የመሣሰሉ 15 ታዋቂ ግለሰቦችን ያቀፈው ‘የአበው አማካሪ ምክር-ቤት’ አንዱ አባል በመሆን የኅብረቱ አባል ድርጅቶች ኅብረቱ በተቋቋመበት መንፈስ የተጣለበትን አገራዊ ኃላፊነትና አደራ እንዲወጣ በኅብረቱ የሸንጎ ስብሰባዎች ላይ በመገኘት ጭምር ታዛቢ በመሆንና ምክራችውን በመለገስ ድርሻቸውን ተወጥተዋል።

ለኢትዮጵያ አገራቸው አንድነትና ለሕዝባቸው እኩልነት ዕድሜ-ልካቸውን የታገሉት ክቡር ኮ/ል አስናቀ እንግዳ የተዋጣላቸው ፀሐፊና ደራሲም ነበሩ። በየጊዜው በሚከሰቱ ወቅታዊ ሁኔታዎች ላይ ካወጧቸው ጽሑፎች በተጨማሪ 1ኛ. አውክና ሰጥ-አርጋቸው፣ 2ኛ. ማነው በደለኛው 3ኛ. ከነበልባል ወደ ረመጥ 4ኛ. ዐረባዊ አፄነት 5ኛ. ሃሣዊ መሲህ 6ኛ. ሸክም የማይከብደው ሕዝብ 7ኛ. ዘመን ያልሻረው የሴቶች አበሳ 8ኛ. ማነው በደለኛ ክፍል ሁለት 9ኛ. የሐይማኖት እምነቴ የተሰኙ መጻሕፍትን ደርሰው ለንባብ አብቅተዋል።



በፖለቲካው መስክ ከነበሯቸው ግንባር-ቀደም ተሣትፎዎች በተጨማሪ የተጣሉትን በማስታረቅ፣ የተራራቁትን በማቀራረብ ረገድ ብዙ ውለታ ሠርተዋል።

ለሐይማኖታቸው በነበራቸው የማይናወጥ እምነታቸው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋኅዶ ቤተ-ክርስቲያን እንዳትከፋፈል የሚችሉትን ሁሉ አድርገዋል። የተወለዱበትና ከፀረ-ፋሽስት የአርበኝነት እንቅስቃሴ ጀምሮ የታገሉበት የጎንደር ክፍለ-አገር ሕዝብ በማኀበራዊ ደረጃ እራሱን እንዲረዳ የጎንደር ኅብረት ተጠናክሮ እንዲቀጥል ከፍትኛ አስተዋጽዖ አደርገዋል።




ክቡር ኮ/ል አስናቀ እንግዳ ቆራጥ አርበኛና መንፈሰ-ጠንካራ የፍትኅና የእኩልነት ታጋይ ብቻ አልነበሩም። ፍቅረ-ንዋይና ሙስናን፣ የሥልጣን ብልግናንና አድልዖን፣ አድር-ባይነትንና ታይታን፣ አጎብዳጅነትንና ከንቱ ውዳሴን አጥብቀው የሚጠሉና የሚጠየፉ፣ ሕይዎታቸውን ከአጉል ልማዶች አጽድተው በከፍተኛ ሥነ-ሥርዓትና ሥነ-ምግባር የመሩ፣ ታማኝነትን፣ ቀጥተኛነትን፣ ቅንነትን፣ ታታሪነትን፣ በቃላቸው መገኘትንና ለሃቅ መቆምን የሕይዎታቸው መርኆዎች አድርገው የኖሩ፣ ባኅላዊ መሠረታቸውን ሣይለቁ እራሣቸውን ለአዲስ አስተሳሰብ ያዘጋጁ፣ ባለ ብሩኅ አእምሮና አርቆ አስተዋይ፣ እራሣቸውን ለማሻሻል ሁል-ጊዜ የሚጥሩ፣ እጅግ ሲበዛ ርኅሩኅ፣ ደግና ለጋስ፣ ቆፍጣናና ኩሩ አገር-ወዳድ ኢትዮጵያዊ የጦር መኮንን ነበሩ።

ክቡር ኮ/ል አስናቀ እንግዳ ከጥቂት ዓመታት በፊት ቀድመዋቸው በሞት ከተለዩአቸው ውድ ባለቤታቸው ከወ/ሮ አበባ ንጉሤ ትርጋለም አስናቀን፣ አስካለ-ማርያም አስናቀን፣ ጽጌ-ማርያም አስናቀን፣ ኄትነት አስናቀን፣ መቅደስ አስናቀንና ውበት አስናቀን አፍርተዋል።




አፍርተዋል። የዘጠኝ የልጅ-ልጆች አያትና የሁለት የልጅ-ልጅ-ልጆች ቅድመ-አያትም ነበሩ። በተጨማሪም ከአብራካቸው እንደወጡ የሚቆጥሯቸውና እንደ ልጆቻቸው የሚያስቡላቸውና የሚወዷቸው እነሱም ከልብ የሚወዷቸውና የሚያከብሯቸው ሥፍር-ቁጥር የሌላቸው የመንፈስ ልጆች ነበሯቸው።





ክቡር ኮ/ል አስናቀ እንግዳ ከተወሰኑ ዓመታት ወዲኅ ባደረባቸው የጤና መታወክ ምክንያት በሕክምና ሲረዱ ቆይተው በቨርጂኒያ ግዛት ውስጥ በአርሊንግተን ማገገሚያ ሥፍራ እሁድ ግንቦት ፳፩ ቀን ፪ ሽህ ፱ ዓ/ም በመቶ አራተኛ ዓመታቸው ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተዋል።





*‘መልካሙን ገድል ታግያለሁ፣ሩጫየን ጨርሻለሁ፣ ሐይማኖቴን ጠብቄአለሁ።’ ፪ ጢሞ. ም/ፍ ፬ ቁ.፯*